9ኛ ዓመት ቁጥር 16
9th Year No. 16

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th April, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 6.60
Unit price 6.60

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር103/ 1996
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ አዋጅ

Content

Proclamation No. 103/2004
The Amhara National Regional State Excise Tax Procalamtion

አዋጅ ቁጥር103/1996
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤክሳይዝ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ

የክልሉን መንግሥትን ገቢ ለማሳደግ በአንዳንድ የተመረጡ ዕቃዎች ላይ የማምረቻ ወጪ አንድ ክፍል ሆኖ የሚቆጠር የኤክሳይዝ ታክስ መጣል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ ታክስ የቅንጦት እንዲሁም መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ፍላጎታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች ላይ እንዲጣል ማድረግ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፣

ታክሱ የጎበረተሰቡን ጤና በሚጎዱ እና ማኅበራዊ ችግር በሚያስከትሉ ዕቃዎች ላይ መጣሉ አጠ ቃቀሙን በመቀነስ ረገድ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው፣

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ - መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና (11) ድንጋጌዎች መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

Proclamation No. 103/1996
A Proclamation Issued for the Excise Tax in the Amhara National State

WHEREAS, to improve the Regional Government revenue it has become necessary to impose excise tax payable on selected goods;

WHEREAS, it is believed that this tax should be imposed on luxury goods and basic goods whose demand inelastic;

WHEREAS, it is believed that imposing the tax on goods that are hazardous to health and which are cause to social problems has a benefit to reducing the consumption of same thereof;

NOW, THEREFORE, in accordance with the provisions of Article 49 Sub-Article 3(1) and (11) of the Revised Constitution of the Amhara National Region, the following is hereby proclamed.

ክፍል አንድ

ጠ ቅ ላ ላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 103/19969.ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ሰው»ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

2. «ድርጅት» ማለት በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሕግ የተቋቋመና የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው::

3. «ንፁህ አልኮል» ማለት ጥራቱ 80 ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አልኮል ማለት ነው::

4. «አልኮል» ማለት ኤሲል አልኮል ነው::

5. «የታክስ ባለሥልጣን» ማለት በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የተቋቋሙ የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው::

6. «የዕቃ መጋዘን» ማለት የታክሱ ባለሥልጣን በሚፈቅደው መሠረት የሚጠበቅና ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ የሚቀመጥበት ቤት ወይም ሥፍራ ነው::

7. «የማምረቻ ወጪ» ማለት ለምርት ተግባር በቀጥታ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችና የጉልበት ዋጋ ፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብዓቶች ወጪ እና አቨር ሄድ ወጪ ሲሆን፣ ለማምረቻ መሣሪያዎች የሚታሰበውን የእርጅና ቅናሽ አይጨምርም::

8. «ታክስ ከፋይ» ማለት የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ነው::

9. «ቢሮ» እና «ቢሮ ኃላፊ» ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው::

PART ONE

General

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Excise Tax Proclamation No. 103/2004."

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1. "Person" means a physical or juridical person.

2. "Enterprise" means any public enterprise, which is established in law under the ownership of the Regional Government and carries out business activities.

3. "Pure Alcohol" means alcohol of purity of 80 degrees or more.

4. "Alcohol" means Ethyl Alcohol.

5. "Tax Authority" means Revenue Authorities established at various levels in the Region.

6. "Bonded Warehouse" means the building or place destined for storage of specified goods before the tax is paid, secured in accordance with requirements of the Tax Authority.

7. "Cost of Production" means direct labour and raw material cost in the production process, cost of indirect inputs and overhead costs, but does not include depreciation costs of machineries.

8. "Taxpayer" means a person liable to pay Excise Tax.

9. "Bureau" and "Bureau Head" means the Bureau of Finance and Economic Development, and Head of this Bureau respectively.

3. የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተዘረዘሩት ዕቃዎች ላይ ነው።

ክፍል ሁለት
የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ልክ፣ የስሌቱ መሠረትና አከፋፈል

4. የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ልክ

ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩት ዕቃዎች በአገር ውስጥ ሲመረቱ፣ በሠንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

5. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት

በአገር ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች ታክሱ የሚሠላበት ዋጋ የማምረቻ ወጪው ይሆናል።

6. የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል

1. የኤክሳይዝ ታክስ በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ በአምራቹ ይከፈላል።

2. የክፍያው ጊዜ፣

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሠረት የተለየ ውሣኔ ካልተሰጠ በስተቀር በሠንጠረዡ የተመለከቱት ዕቃዎች በአገር ውስጥ ሲመረቱ ከተመረቱበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል።

ለ/ አምራቹ የተመረቱትን ዕቃዎች የታክሱ ባለሥልጣን በሚፈቅደው የዕቃ መጋዘን ውስጥ ታክስ ሳይከፈል ለማስቀመጥ ፈቃድ የጠየቀ እንደሆነና የታክሱ ባለሥልጣንም ይህንኑ ከፈቀደ በዚህ ሁኔታ በተቀመጡት ዕቃዎች ላይ ታክሱ ዕቃዎቹ ከመጋዘን እንደወጡ ወዲያውኑ ይከፈላል።

ሐ/ የታክሱ ባለሥልጣን የአምራቹ የሥራ እንቅስቃሴ የዕቃ መጋዘን የሚያስፈልገው ሆኖ ሲያገኘው እንዲህ ያለውን መጋዘን እንዲያቋቁም ይፈቅድለታል። የዕቃ መጋዘኑ ሥራውን የሚመራበትን ሁኔታም በመመሪያ ይወስናል። ስለሆነም የታክሱ ባለሥልጣን ወኪል በሥፍራው ካልተገኘና ካልተቆጣጠረ በስተቀር ምንም ዓይነት ዕቃ በመጋዘን ውስጥ ለማስቀመጥ ወይም ከመጋዘኑ እንዲወጣ ለማድረግ አይቻልም።

3. The Scope of the Proclamation

This Proclamation applies on goods listed in the Schedule attached to this Proclamation.

PART TWO
The Rate, Base and Payment of Excise Tax

4. Rate of Excise Tax

The Excise tax shall be paid on goods mentioned under the Schedule attached to this Proclamation when produced locally at the rate prescribed in the Schedule.

5. Base of Computation of Excise Tax

The cost of computation of excise tax shall be the cost of production in respect of goods produced locally.

6. Payment of Excise Tax

1. The producer shall pay the Excise tax in respect of goods produced locally within the time prescribed under Sub-Article (2) of this Article.

2. Time of Payment:

A. Unless decided otherwise, as provided for under Sub-Article 2(b) of this Article, the excise tax on goods specified under the Schedule shall be payable when produced locally, not later than 30 days from the date of production.

B. Where the tax payer requests for permission to deposit goods produced in a bonded warehouse without payment of tax and if the request is approved by the Tax Authority the payment of the tax on such goods so deposited shall be effected at the time they are being removed from the Bonded warehouse;

C. If the Tax Authority believes that the activity of the taxpayer requires a Bonded Warehouse may give him permission to establish such Bonded Warehouse. The conditions under which the Bonded Warehouse operates shall also be laid down by directive to be issued by the Tax Authority. No goods shall therefore be deposited in or removed from a Bonded Warehouse except in the presence and under the control of a representative of the Authority.

መ/ አምራቹ ተገቢ የሆኑትን የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶች ሳይዝ የቀረ እንደሆነ ወይም የየወሩን የሂሳብ መግለጫ ያላቀረበ እንደሆነ ወይም በዚህ አዋጅ ውስጥ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ወይም ያቀረበው የሂሳብ መግለጫ በምርመራ ትክክለኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ታክሱ እስኪከፈል ድረስ የታክሱ ባለሥልጣን አምራቹ ማንኛውንም ዕቃ ከማምረቻው ቦታ ወይም ከዕቃው መጋዘን ውስጥ እንዳያወጣ ለመከልከል ይችላል።

7. **የኤክሳይዝ ታክስ አወሳሰን**

1. የታክሱ ባለሥልጣን የአምራቹ የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶች በሚገባ መያዛቸውንና አምራቹም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(ለ) በተመለከተው መሠረት የሚያቀርበው የየወሩ የሂሳብ መግለጫ ትክክል መሆኑን ሲቀበል በሂሳብ መግለጫው በተመለከተው መሠረት የተከፈለው ታክስ ትክክለኛ ሆኖ ይቆጠራል።

2. የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሂሳብ ከመረመረ በኋላ ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ይሰጣል።

3. የታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ በማናቸውም ምክንያት በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ካላገኙ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ካልቀረቡ ወይም የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች ከሌሉ የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን ባለው መረጃ መሠረት በማምት ይወስናል።

4. የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሳኔ በማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ለታክስ ከፋዩ ይላካል። የውሳኔ ማስታወቂያ የመላኩ አፈፃፀም በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም. በተሻሻሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

D. Where a producer fails to keep proper accounts and records or fails to submit a monthly declaration or pay the tax within the time limit prescribed in this Proclamation or submits a declaration which upon investigation is found incorrect the Tax Authority shall be empowered to forbid the producer to remove any good from the place of production or Bonded Warehouse.

7. **Assessment of the Excise Tax**

1. If the Tax Authority accepts that the books and records maintained by the producer are properly kept and that the monthly declaration submitted by him, pursuant to Article 8(b) of this Proclamation is correct the tax paid in accordance with the monthly declaration shall be considered accurate.

2. If, after review by the Tax Authority, it appears that a person has understated his tax obligation, the Authority shall issue an additional assessment.

3. The authority shall make an assessment based on the information it has approximately when the taxpayer books of accounts and supporting documents fail to be accepted by any means by the tax authority or fails to be submited when the tax authority asks or books of accounts and supporting documents are absent.

4. The assessment made shall be prepared in an assessment notification and be delivered to the taxpayer. Delivery of the assessment notification shall be made in accordance with the provisions of Income Tax Proclamation No. 76/2002 of the Region.

5. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ የሰጠ እና የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ እንዲከፍል የተጠየቀውን ተጨማሪ ታክስ ያልከፈለ ወይም በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በአንቀጽ 18 መሠረት ይግባኝ ያላቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው::

5. If the Authority makes an additional assessment under Sub-Article (2) and within 30 days of the notice and demand, the person assessed does not pay the additional assessment or appeal the assessment as provided under Article 18, the person is in default.

6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ታክስ ከፋዩ ታክሱን አስታውቆ ከከፈለበት የበጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን ልክ ወስኖ ቀሪ ሂሳብ መኖሩን ካላስታወቀ የተከፈለው ታክስ በቂና የመጨረሻ ይሆናል:: ሆኖም ታክስ ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታወቂያ ያቀረበ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በማናቸውም ሌላ ሕግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ታክሱን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል::

6. If the Tax Authority fails to assess the tax and notify the tax payer of the amounts still due within five years from the date of declaration and payment of the tax by the tax payer in accordance with Article 6 of this proclamation, the tax so paid shall be suffice and final. In case, where the taxpayer has not declared his income or has submitted a fraudulent declaration, no time limit provided in any other law shall bar the assessment of the tax by the Tax Authority.

ክፍል ሦስት

የታክስ አሰባሰብ አፈፃፀም

PART THREE

Collection Enforcement

8. የታክስ ከፋዩ ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ከተጠቀሱት ግዴታዎች በተጨማሪ ማናቸውም የኢክሳይዝ ታክስ ከፋይ:-

ሀ/ አግባብ ባለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና የታክስ ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ዓይነት የሂሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሠነዶችን ይይዛል::

ለ/ በታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ቅፅ ላይ ታክሱን በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ሞልቶ በየ30 ቀኑ ለታክስ ባለሥልጣኑ ያቀርባል::

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የታክስ ባለሥልጣኑ የሚጠይቀውን ይፈፅማል::

መ/ የታክስ ባለሥልጣኑ ወኪል በሥራ ቦታው በመገኘት ስለታክስ አሰባሰብ ለሚያደርገው ቁጥጥር አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ አሟልቶ ያቀርባል::

8. Obligations of the Tax payer

In addition to the obligations specified in the other provisions of this Proclamation, every taxpayer shall:

a) Maintain books of accounts and supporting document in accordance with proper accounting principles and in a manner acceptable to the Tax Authority.

b) Submit every 30 days to the Tax Authority in a form which shall be supplied by said Authority a declaration containing such information as may be necessary for proper collection of the tax.

c) Comply fully with requirements of the inspection of his premises by the delegate of the Tax Authority in accordance with Sub-Article 2 of Article 9 of this Proclamation.

D) Comply fully with the requirements of the inspection of his premises by the delegate of the Tax Authority.

ሠ/ የሥራውን ዓይነትና የሥራውን አድራሻ እንዲሁም ሥራውን ሲጀምርም ሆነ ሲያቋርጥ፣ ሁኔታውን ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ያሳውቃል::

ረ/ ሥራውን ሲያቋርጥ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ ሥራውን ባቋረጠ በ30 ቀናት ውስጥ አጠናቆ ይከፍላል::

9. የታክሱ ባለሥልጣን ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች ከተጠቀሱት በተጨማሪ የታክሱ ባለሥልጣን የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል:-

1. ይህንን አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈፀም፣

2. ታክስ ከፋዩን ወይም የሂሳብ መዛግብትን እና ሰነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የታክሱ ባለሥልጣን የሥራ ሰዓቶች እና በጽ/ቤቱ ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሰነዶች እንዲያቀርብ የማድረግ፣

3. ሀ/ የምርት ተግባር ወይም የሽያጭ ሥራ ስለመካሄዱ ወይም ለታክሱ አከፋፈል የሚረዳ ማስረጃ ስለመኖሩ ሲጠራጠር ወይም ይህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጡት ደንቦች እና መመሪያዎች በሚገባ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በታክስ ከፋዩ መደበኛ የሥራ ሰዓቶች፣

ለ/ ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በመተላለፍ ጥፋት የተፈፀመ ለመሆኑ ሲጠራጠር በማንኛውም ጊዜ፣

ወደ ታክስ ከፋዩ የሥራ ቦታ ወይም የዕቃ መጋዘን ወይም ምርቱ ይገኝበታል ተብሎ ወደሚገመተው ማናቸውም ሥፍራ የመግባትና ሁኔታዎችን የማጣራት፣ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ ተገቢውንም እርምጃ የመውሰድና

4. በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ለታክስ ከፋዩ የማስታወቅ፣

E) Immediately communicate to the Tax Authority the type and address as well as the commencement and termination date of his business.

F) Pay in full the tax due within 30 days from the date of termination where such business is terminated.

9. Power of the Tax Authority

In addition to the powers specified in the other provisions of this Proclamation, the Tax Authority shall have the following powers and duties;

1. The implementation and enforcement of this proclamation in the Region;

2. Requiring the person or any employee who has access to or custody of any information, records or books of account to produce the same and to attend during normal office hours at any reasonably convenient tax office and answer any questions relating thereto;

3. Enter business premises or stores of the tax payer or to any place suspected to be storage of the products, inspect, collect information and take appropriate measures;

a) During the regular working hours of the tax payer where it suspects that production or sale of goods is carried on or there is information that may be necessary for the proper assessment of the tax, and to ensure the observance of this Proclamation and Regulations issued for the implementation of this Proclamation;

b) At any time where it suspects that an offense resulting from the violation of the provisions of this Proclamation or regulations issued for the implementation of the Proclamation has been committed.

4. Notify the tax payer the additional tax to be paid in accordance with this proclamation;

5. ማዘጋጃ ቤት፣ ድርጅት፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውንም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ጨምሮ ማንኛውም ሰው ስለታክስ ከፋዩ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ዝርዝር እንዲገልፅ የማድረግ::

10. ታክስን ለመሰብሰብ ሀብት ስለመያዝ

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 ወይም በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የዚህን ታክስ ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ታክስ እና ንብረቱን ለመያዝ ለተደረገው ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ለማድረግ ሕጋዊ ሥልጣን ይኖረዋል::

2. ለዚህ ክፍል አፈፃፀም «መያዝ» በማናቸውም መንገድ መያዝን እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ የሚፈለግበት ሰው የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል:: በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 6 በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው:: የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ኃይል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል:: ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ10 ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል:: ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በሚታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል::

3. ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የታክስ ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የታክስ ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል::

5. Requiring any person including municipality, body, financial institution, department or agency of Federal or Regional Government to disclose particulars of any information or transactions.

10. Seizure of Property to Collect Tax

1. Subject to Sub-Article (4) of this Article, if any person liable to pay any tax imposed by this proclamation is in default under Article 7 Sub-Article (4) or Article 18 Sub-Article (2), it shall be lawful for the Authority to collect such tax and such further amount as shall be sufficient to cover the expenses of the seizure by seizing any property belonging to such person.

2. For purposes of this Section, the term "seizure" includes seizure by any means, as well as collection from a person who owes money or property to the person liable for Excise tax. Except as provided in Sub-Articles (3) and (6) a seizure shall extend only to property possessed and obligations existing at the time the seizure is made. The Authority may request a police officer to be present during the seized. Where the Authority seizes any property as provided hereinabove, it shall have the right to sell the seized goods at public auction or in any other manner approved by the Authority not less than 10 days after the seizure, except that when the goods seized are perishable the Authority can sell the goods after any reasonable period having regard to the nature of the goods.

3. Whenever any property on which seizure had been made is not sufficient to satisfy the claim for which seizure is made, the Authority may, thereafter and as may be necessary, proceed to seize other property liable to seizure of the person against whom the claim exists until the amount due from such person together with all expenses, is fully paid.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረት መያዝ የሚቻለው የታክሱ ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ በፅሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል። በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ30 ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል።

5. የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ እና በንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክሱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ከቀረበና ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል።

6. ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት።

7. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በታክስ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብት ለታክሱ ባለሥልጣን የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት።

8. ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የታክስ ዕዳ መጠን (በታክሱ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ) ሊያልፍ አይችልም።

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን 50 በመቶ በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።

4. Seizure may be made under Sub-Article (1) on property of any person in default with respect to any unpaid tax only after the Authority has notified such person in writing of the intention to make such seizure. The notice shall be delivered not less than thirty (30) days before the day of the seizure.

5. If the Authority makes a finding that the collection of the tax is in jeopardy, demand for immediate payment of such tax may be made by the Authority and, on failure or refusal to pay the tax, collection thereof by seizure shall be lawful without regard to the 30-day period provided in Sub-Article (1) and the 30-day provided in Sub-Article (4).

6. If a seizure has been made or is about to be made on any property, any person having custody or control of any books or records containing evidence or statements relating to the property subject to seizure shall on demand of the Authority, exhibit such books or records to the Authority.

7. Any person in possession of (or obligated with respect to) property subject to seizure on which seizure has been made shall, on the demand of Authority, surrender such property (or discharge such obligation) to the Authority, except such part the property as is, at the time of such demand, subject to a prior secured claim of creditors and subject to attachment or execution under any judicial process.

8. Any person who fails or refuses to surrender a property subject to seizure, on demand of the Authority, shall be personally liable to the government in a sum equal to the value of the property not so surrendered, but not exceeding the amount of for the collection of which seizure has been made (together with costs and interest on such sum).

9. In addition to the personal liability imposed by Sub-Article (8), if the failure or refusal to surrender is without reasonable cause, such person shall be liable for an additional charge equal to fifty percent (50%) of the amount recoverable under Sub-Article (8)

10. በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት ያስረከበ ወይም በታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከታክሱ ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል።

10. Any person in possession of property who surrenders or makes payment in accordance with this Article shall be discharged from any obligation or liability to the delinquent person or to any other person arising from such surrender or payment.

11. በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

1. ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክሱ ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ የታክሱ ባለሥልጣን የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

2. ማናቸውም ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የታክሱ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የፅሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልፅ ማስጠንቀቂያ ለተመዘገበው ሰው ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ለንብረት መዝጋቢው ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ሀብት ባልተከፈለው የታክስ ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል። ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል።

11. Preferential Claim to Assets

1. From the date on which tax becomes due and payable under this Proclamation, subject to the prior secured claims of creditors, the Authority has a preference claim upon the assets of the person liable to pay tax until the tax is paid.

2. Where a person is in default of paying tax, the Authority may, by notice in writing, inform that person of the Authority's intention to apply to the Registering Authority to register a security interest in any asset, which is owned, by that person, to cover any unpaid tax in default, together with any expense incurred in recovery proceedings.

3. If the person on whom a notice has been served under Sub-Article (2) of this Article fails to pay the amount specified in the notice within 30 days after the date of service of the notice, the Authority may, by notice in writing direct the Registering Authority that the asset, to the extent of the defaulter's interest therein, shall be the subject of security for the total amount of unpaid tax.

4. Where the Authority has served a notice on the Registering Authority under Sub-Article (3), the Registering Authority shall without fee, register to the notice of security as if the notice were an instrument of mortgage over or charge on, as the case may be such asset, and such registration shall, subject to a prior mortgage or charge, operate while it subsists all respects as a legal mortgage over or charge on the asset to secure the amount due.

12. ታክስ ከፋዩ ስላላው ጥበቃ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 እና 11 መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው፣ እና የሚመዘገበው በታክሱ ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል። ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም። የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል።

13. የተረካቢ ግዴታ

1. በዚህ አንቀጽ ውስጥ «ተረካቢ» ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የታክስ ከፋዩን ሀብት በተመለከተ፣

   ሀ/ ከፍርድ ቤት ውጪ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተረካቢ፣

   ለ/ በኪሣራ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ባለአደራ፣

   ሐ/ መያዣ በይዞታው ሥር የሚገኝ ሰው፣

   መ/ የሞተን ሰው ንብረት የሚያስተዳድር ወይም

   ሠ/ በሕግ ችሎታ የሌለውን ሰው የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ሰው ነው።

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረት ተረካቢ ሆኖ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር የተደረገ ተረካቢ ከተሾመበት ወይም ንብረቱ በይዞታው ሥር ከተደረገበት ከሁለቱ ከቀደመው ቀን ጀምሮ በ14 ቀን ጊዜ ውስጥ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር ያለ መሆኑን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

3. የታክሱ ባለሥልጣን ንብረቱ በተረካቢው ይዞታ ሥር ያለ ሰው የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ለተረካቢው በፅሑፍ ያስታውቃል።

12. Taxpayer Safeguards

Any property seized under Part 3 of this Proclamation shall be seized, held and accounted for only by the Authority. No other agency of the government may require the property seized under this Part to transferred or given over to it for any cause whatsoever. If any property seized under this Part is sold, any portion of the proceeds in excess of the person's liabilities shall be returned promptly to the owner of the property.

13. Duties of Receivers

1. In this Article, "receiver" means a person, who with respect to an assets in Ethiopia of a taxpayer, is:

   a) A receiver appointed out of court or by a court;

   b) A trustee for an unrehabilitated insolvent;

   c) A Mortgage in possession;

   d) An executor of a deceased estate; or

   E) Any other person conducting a business on behalf of a person legally incapacitated.

2. A receiver shall, in writing, notify the Authority within 14 days after being appointed to the position or taking possession of an asset in Ethiopia, whichever first occurs.

3. The Authority may, in writing, notify a receiver, or the amount which appears to the Authority to be sufficient to provide for tax which is or will become payable by the person whose assets are in the possession of the receiver.

4. ተረካቢው፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በታክስ ባለሥልጣኑ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ወይም ከማስታወቂያው በኋላ በስምምነት የተደረሰበትን ሌላ የገንዘብ መጠን ከንብረቱ ሽያጭ ላይ ቀንሶ ለብቻው ያስቀምጣል።

ለ/ ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ልክ የተረከበው ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው ለሚፈለገው የታክስ ዕዳ ተጠያቂ ይሆናል።

ሐ/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ከታክስ ቀደምትነት ያለውን ማናቸውንም ዕዳ ሊከፍል ይችላል።

5. ተረካቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰውን ታክስ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ተቀንሶ ለብቻው እንዲቀመጥ የተደረገውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ለተጠቀሰው ታክስ ካላዋለ ተቀንሶ ለብቻ በተቀመጠው ገንዘብ ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል።

14. ለውጦችን ስለማስታወቅ

ማናቸውም ታክስ ከፋይ፡-

1. ስሙ፣ አድራሻው፣ የንግድ ሥራው ቦታ፣ አደረጃጀቱ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋንኛው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናቸው ተግባራት ዓይነት፣

2. ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበት አድራሻ ወይም ስም፣ የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት።

ክፍል አራት

ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሥርዓት

15. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በቢሮ ኃላፊው ይሰየማሉ።

16. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊው ወይም እርሱ ለሚወክለው ሆኖ፣

4. A receiver:

a) Shall set aside, out of the proceeds of sale of an asset, the amount specified by the Authority under Sub-Article (3) of this Article thereof or such lesser amount as is subsequently agreed on by the Authority.

b) Is liable to the extent of the amount set aside for the tax of the person who owned the asset.

c) May pay any debt that has priority over the tax referred to in this Article notwithstanding any provision of this Article.

5. A receiver is personally liable to the extent of any amount required to be set aside under Sub-Article (4) for the tax referred to in Sub-Article (3) if, and to the extent that, the receiver fails to comply with the requirements of this Article.

14. Notification of Changes

Every taxpayer shall notify the Authority, in writing of:

1. Any change in the name, address, place of business, constitution, or nature of the principal taxable activity or the activities of the person; and

2. Any change of address from which, or name in which a taxable activity is carried on by the taxpayer, with in 5 days of the change occurring.

PART FOUR

Appeal Procedure

15. Review Committee

The Head of the Bureau shall appoint members of the Review Committee.

16. Powers and Duties of the Review Committee

1. The Committee being accountable to the Head of the Bureau shall have the following duties;

ሀ/ በታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የታክስ ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን የመመርመርና የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣

ለ/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም የፅሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች የመሰብሰብ፣

ሐ/ በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከታክሱ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት፣

መ/ የቢሮ ኃላፊው ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው የሰጠው የታክስ ውሳኔ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ይኖረዋል::

2. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ከታክስ ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው::

3. የታክሱ ባለሥልጣን ኃላፊ የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ ሊያፀድቅ ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለፅ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል:: ሆኖም ኮሚቴው የተለየ ሃሳብ ይዞ ካልቀረበ ኃላፊው የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል::

17. መቀጫን ስለማንሳት

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል::

18. ስለይግባኝ

1. በታክሱ ባለሥልጣን የተላለፈውን የተጨማሪ ታክስ ውሳኔ የሚቃወም ማናቸውም ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በቢሮ ኃላፊው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን ተጨማሪ ታክስ 50% (አምሳ በመቶ) ባለሥልጣኑ ዘንድ በማስያዝ ለሚመለከተው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው::

a) To examine and recommend on all applications submitted by tax payers for compromise of penalty and interest and on the tax assessed;

b) To gather any written evidence or information relevant to the matter submitted;

c) To summon any person who directly or indirectly has dealt with the assessment, to appear before it for questioning him about the case under its investigation; and

d) To review determinations made by the by Head of the Bureau or by a person assigned by him for accuracy, completeness, and compliance with this proclamation.

2. The Committee shall only review applications submitted to it within 10 days of receipt of tax assessment notification.

3. The Head of the Tax Authority may approve the recommendations or remand the case, with his observations, to the committee for further review. However, the Head shall give a final decision where the committee fails to present a defferent recommendation.

17. Waiver of Penalty

The Review Committee may recommened on waiving administrative penalities in full or in part in accordance with the directivies issued by the Bureau, as appropriate.

18. Appeal

1. Any person who objects to an additional assessment made by the Authority has the right to appeal, within 30 days from the receipt of that assessment notification, or from the date of decision made by the Bureau Head to the Tax Appeal Commission by depositing in cash with the Authority an amount equal to 50% of the additional tax assessed.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ የወሰንበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ ጥፋተኛ ነው::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ የተወሰነው ተጨማሪ ታክስ ትክክለኛና የመጨረሻ ሆኖ ወዲያውኑ ተከፋይ ይሆናል::

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም ስለይግባኝ የተደነገጉ አንቀፆች እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑ ታክሶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ይግባኞች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

19. የማስረዳት ኃላፊነት

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው ውሳኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ኃላፊነት የተወሰነውን ታክስ ወይም የባለሥልጣኑን ውሳኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል::

ክፍል አምስት

አስተዳደራዊ ቅጣቶች

20. የታክስ ማስታወቂያን በጊዜው ባለማቅረብ ስለሚፈፀም ቅጣት

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም ከተወሰነው በስተቀር፣ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ፣ ያልተከፈለውን ታክስ 5% (አምስት በመቶ) 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል::

2. የታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ባለበት ወር ወይም የወሩ ከፊል በሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ እስከ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) የሚደርስ ይሆናል::

2. If a person appeals in accordance with Sub-Article (1) of this Article and the Tax Appeal Commission determines his tax liability, that person is in default unless he pay the additional assessment determined by the Tax Appeal commission within thirty (30) days of the decision of the Commission.

3. If no appeal is made within the period prescribed in Sub-Article(1) of this Article, the Additional assessment of the tax made by the Authority shall be deemed to be correct and final and shall be immediately payable.

4. Without prejudice to sub-Article (1) of this Article, the provisions of the Income Tax Proclamation concerning appeals shall, mutatis mutandis, apply to appeals regarding taxes imposed by this Proclamation.

19. Burden of Proof

The burden of proving that an assessment is excessive or that a decision of the Authority is wrong is on the person objecting to the assessment or decision.

PART FIVE

Administrative Penalties

20. Penalties for Late Filing

1. Except as otherwise provided in this Proclamation a person who fails to file a timely return is liable for penalty equal to 5 percent of the amount of the underpayment for each month (or portion thereof) during which the failure continues, up to 25% (twenty five percent) of such amount.

2. The penalty under Sub-Article (1) of this Article reaches 50,000 Birr for the first month (or portion thereof) in which no return is filed.

3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው።

4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም

ሀ/ ብር 10,000 (አሥር ሺህ)

ለ/ በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% (አንድ መቶ ፐርሰንት)

21. ዘግይቶ በተከፈለ ታክስ ላይ ስለሚታሰብ ወለድ

1. መከፈል በነበረበት ወር ላልተከፈለ ታክስ፣ መከፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ታክሎበት ይሆናል።

ክፍል ስድስት

የወንጀል ቅጣቶች

22. በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ-ሥርዓት

በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ይሆናል።

23. ሕግን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል

ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ታክስ ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል። ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል 5 መሠረት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ5 ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል።

3. For the purposes of this Article, an underpayment of tax is the difference between the tax required to be shown on the return and the amount of tax paid by the due date.

4. In any event the penalty may not be less than the smaller of the two amounts:

a. 10,000 Birr (ten thousand Birr);

b. 100% (one hundred percent) of the amount of tax required to be shown on the return.

21. Late Payment Interest

1. If any amount of tax is not paid by the due date, the person liable is obliged to pay interest on such amount for the period from the due date to the date the tax is paid.

2. The interest rate under Sub-Article (1) of this Article is set at 25% (twenty five per cent) over and above the highest commercial lending interest rate that prevailed during the preceding quarter.

PART SIX

Criminal Penalities

22. Procedure in Tax Offence Cases

A tax offence under this Section is a violation of the Criminal Law of Ethiopia and shall be charged, prosecuted, and appealed in accordance with the Criminal Procedure Code of Ethiopia.

23. Tax Evasion

A person who evades the declaration or payment of tax, commits an offence and, in addition to any penalty under Part 5, may be prosecuted and, on conviction, be Subject to a term of imprisonment of not less than five (5) years.

24. የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ

1. ማናቸውም ታክስ ከፋይ፡-

ሀ/ ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ፣ ወይም

ለ/ ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣ የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።

2. የተሳሳተ መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነ እንደሆነ፡-

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1,000 በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 10,000 በማያንስ እና ከብር 20,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከ3 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

ለ/ አንሶ እንዲከፍል የሚደረገው ታክስ ከብር 1,000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 20,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

3. የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ፣

24. Making False or Misleading Statements

1) A taxpayer who:

(a) Makes a statement to a tax officer of the Authority that is false or misleading in a material particular, or

(b) Omits from a statement made to an officer of the Authority any matter or thing without which the statement is misleading in a material particular, commits an offence and is liable on conviction.

2) Where the statement or omission is made without reasonable excuse:

(a) And if the inaccuracy of the statement were undetected may result in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, to a fine of not less than 10,000 Birr and not more than 20,000 Birr, and imprisonment for a term of not less than one (1) year and not more than three (3) years; and

(b) If the underpayment of tax is in an amount exceeding 1,000 Birr to a fine of not less than 20,000 Birr and not more than 100,000 Birr and imprisonment for a term of not less than three (3) years and not more than five (5) years.

3) Where the statement or omission is made knowingly or recklessly;

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1,000 በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት፣

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1,000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 75,000 በማያንስ እና ከብር 200,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል::

25. የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል

1. ማናቸውም ሰው:-

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የታክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናክለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ፣ ወይም

ለ/ የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናክለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ፣ ሲፈረድበት ከብር 1,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል::

2. የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ::

ሀ/ የታክስ ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ለ/ የታክሱ ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ሐ/ የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ፣

(a) And if the inaccuracy of the statement were undetected may result in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, to a fine of not less than 50,000 Birr and not more than 100,000 Birr, or imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years; and

(b) If the underpayment of tax, is in an amount exceeding 1,000 Birr, to a fine of not less than 75,000 Birr and not more than 200,000 Birr or imprisonment for a term of not less than ten (10) years and not more than fifteen (15) years.

25. Obstruction of Tax Administration

1) A person who:

(a) Obstructs or attempts to obstruct an officer of the Authority in the performance of duties under this proclamation, or

(b) Otherwise impedes or attempts to impede the administration of the proclamation, Commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 1,000 Birr and not more than 100,000 Birr, and imprisonment for a term of two (2) years.

2) The following and similar other actions are considered to constitute obstruction.

(a) Refusal to satisfy a request of the Authority for inspection of documents, reports, or other information related to a taxpayer's income producing activities;

(b) Noncompliance with an authority request to report for an interview;

(c) Interference with a taxation officer's right to enter the taxpayer's business premises;

መ/ የሚሰጠውን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያና ሌሎች ጥሪን የተመለከቱ ደብዳቤዎች ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን::

26. ለውጥን ያለማስታወቅ

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 በሚያዘው መሠረት በሁኔታዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ለታክስ ባለሥልጣን ያላስታወቀ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከብር 10,000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ዓመት እሥራት፣

ለ/ በሌሎች ሁኔታዎች ከብር 5,000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በ6 ወር እሥራት ይቀጣል::

27. በታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም በታክስ ባለሥልጣኑ የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተቀጣሪ የነበሩ፡-

ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም

ለ/ ከታክስ በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በታክስ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል::

(D) To be unwilling to accept tax assessment notice and call related letters which is given to him.

26. Failure to Notify Changes

A person who fails to notify the Authority of a change as required by Article 14 of this proclamation commits an offence and is liable on conviction:

(a) Where the failure was made knowingly or recklessly, to a fine of not less than 10,000 Birr and to imprisonment for one year; or

(b) In any other case, to a fine of not less than 5,000 Birr and to imprisonment for six months.

27. Commission of Offences by Tax Officer

1) Any tax officer or former taxation officer employed in carrying out the provisions of this proclamation who:

a) Directly or indirectly asks for, or receives in connection with any of the taxation officer's duties, a payment or reward, whether pecuniary or otherwise, or security for that payment or reward, not being a payment or reward which the officer is lawfully entitled to receive, or

b) Enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing, permit, conceal, or connive at any act or thing whereby the tax revenue is or may be defrauded or which is contrary to the provisions of this proclamation or to the proper execution of the taxation officer's duty, commits an offence and is liable on convction to a fine of not less than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than ten(10) years and not more than twenty (20) years.

2/ የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የተቀጠረ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣

ሀ/ ታክስን በማስፈፀም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ግዴታ ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚያ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስን በማስፈፀም ረገድ ያለውን ሥልጣን ለመጠቀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከሁለት ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል::

3/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ

ሀ/ ማናቸውንም ሰነድ ወይም መረጃ:-

i. ለዚህ አዋጅ ወይም ለማናቸውም ገንዘብ ነክ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣

ii. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዋናው አዲተር፣

iii. መረጃ ለመለዋወጥ፣ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት አግባብ ላላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች፣

iv. በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለክልሉ የፍትህ ቢሮ፣

v. ከዚህ በላይ ላልተገለፀ ለማናቸውም ሕግ አስፈፃሚ መ/ቤት ግዴታውን ለመፈፀም የሚያስችለው መረጃ እንዲሰጠው ከቢሮው በፅሑፍ ሲታዘዝ::

2) A tax officer or former tax officer employed in carrying out the provisions of this proclamation except such information is required by the Commercial Code of Ethiopia to be published in the Trade Gazetta, who:

A) Discloses to any person or that person's representative, any matter in respect of another person, that may, in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the taxation officer's duties under the said provisions, come to the taxation officer's knowledge; or

B) Permits any other person to have access to records in the possession or custody of the authority, except in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the officer's duties under this proclamation or by order of a court;

Commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 10,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than two (2) years and not more than five (5) years.

3/ Nothing in this Article shall prevent a taxation officer from disclosing;

(a) Any document or information to:

i. Any person where the disclosure is necessary for the purposes of this proclamation or any other fiscal law;

ii. The Auditor-General where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law.

iii. The competent authority of the governmet of another country with which Ethiopia has entered into an agreement for the avoidance of double taxation of for the exchange of informaiton, to the extent permitted under the agreement;

iv. The Ethics and Anti-Corruption Commission where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law.

v. A law enforcement agency not described above where the Bureau issues written authorization to make disclosures necessary for the enforcement of the laws under the agency's authority.

ለ/ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አንድን ሰው ለይተው የማይጠቅሱ መረጃዎችን ለማናቸውም በመንግሥት ገቢ ሥራ ላይ ለሚያገለግል ለስታትስቲክስ መ/ቤት ሠራተኛ ከመስጠት አያግደውም::

28. ሳይፈቀድ ታክስ ስለመሰብሰብ

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ታክስ ወይም እንደታክስ የሚታዩ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50,000 የማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ5 ዓመት በማያንስ ከ10 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል::

29. መርዳት ወይም ማበረታታት

ማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ፣ ወይም በሚስጥር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈፅማል:: ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈፀመ ሰው፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል::

30. በድርጅቶች የሚፈፀም ጥፋት

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈፀመውን ጥፋት እንደፈፀመ ተቆጥሮ፣ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደታክስ የሚቆጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ጥፋቱ ከተፈፀመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የታክሱ ባለሥልጣን ለሚፈልገው ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ::

b) Information which does not identify a specific person to any person in the service of the state in a revenue or statistical department where such disclosure is necessary for the performance of the person's official duties.

28. Unauthorized Tax Collection

Any person not authorized to collect tax under this proclamation who collects or attempts to collect tax (on an amount the person describes as tax) commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years.

29. Aiding or Abetting

Any person aids, abets, incites, or conspires with another person to commit a violation of this proclamation also commits a violation of this proclamation. That person may be subject to prosecution and is liable, on conviction, to a fine and imprisonment, not in excess of the amount of fine or period of imprisonment provided for the offence aided or abetted.

30. Offences by Entities

1) Subject to Sub-Article (3), where an entity commits an offence, every person who is a manager of that entity as that time is treated as also having committed the same offence and is liable to a fine and imprisonnment under this Proclamation.

2) Subject to Sub-Article (3), where an entity commits an offence by failing to pay an amount of tax, including an amount treated by this Proclamation as though it were tax, every person who was a manager of that entity as that time or was a manager within six (6) months prior to the date of commission is jointly and severally liable with that entity and that other person to the Authority for the amount.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉት:-

ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፣

ለ/ አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፣ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ ተፈጻሚ አይሆኑበትም::

4/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 አፈፃፀም «ሥራ አስኪያጅ» ማለት የድርጅቱ የሥራ መሪ፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ሰው ነው::

31. በተረካቢዎች የሚፈፀም ጥፋት

1. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፣ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብር 5,000 የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ዓመት እሥራት ይቀጣል::

2. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ለታክስ ክፍያ የሚውለውን ገንዘብ ለይቶ ባለማስቀመጡ ምክንያት በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከገንዘብና እሥራት መቀጫው በተጨማሪ ለይቶ ያላስቀመጠውን የገንዘብ መጠን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል::

32. የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት

1. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 22 እስከ 31 የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈፀም የተፈረደባቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር:-

ሀ/ የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፣

ለ/ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር፣

3) Sub-Articles (1) and (2) do not apply where:

a) The offence is committed without that person's Knowledge or consent; and

b) That person has exercised the degree of care, diligense and skill that a reasonably prudent person would have exercised in comparable circumstances to prevent the commission of the offence.

4) For the implementation of this Article, Sub-Article (1) and (2), "manager" means a director of the Organization, manager or any other officer or a person purporting to act in any of those capacities.

31. Offences by Receivers

1. A person who fails to comply with the requirements of Article 13, Sub-Article (4) commits an offence and is liable on conviction to a fine of 5,000 Birr and to imprisonment for one (1) year.

2. Where a person is convicted of an offence under Sub-Article (1) for failing to set aside an amount as required under Article 13, Sub-Article (4), the court may, in addition to imposing a fine and prison sentence, order the convicted person to pay to the Authority, amount not exceeding the amount which the person failed to set aside.

32. Publication of Offenders' Names

1. The Authority shall from time to time publish by notice in the Gazetta list of persons who have been convicted of offences under any of Article 22 to 31.

2. Every list published in terms of Sub-Article (1) shall specify:

a. The name, address, and principal enterprise of the person:

b. Such particulars of the offence as the Authority may think fit;

ሐ/ ጥፋቱ የተፈፀመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመኖች፣

መ/ ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን፣

ሠ/ በተጨማሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ፣

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

33. የመተባበር ግዴታ

1. ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣኖችና ወኪሎቻቸው በተጨማሪም ድርጅቶች፣ የቀበሌ አስተዳድሮች፣ ማህበራት ሁሉ ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው::

2. ሀ/ በይግባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የተራዘመ የታክስ መክፈያ ጊዜ ካልሰጠ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ታክስ ከፋይን በሚመለከት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ በስተቀር ፈቃድ ሰጪ ማዘጋጃ ቤት፣ የፌዴራል ወይም የክልል መሥሪያ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጣት ወይም ማደስ አይችልም::

ለ/ የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈፀሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ሲሆን፣ ስለዚሁ ያለውን ምክንያት በመዘርዘር በፅሑፍ ለጠያቂው ይሰጣል::

ሐ/ የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመሠረዙ የታክሱ ባለሥልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል::

34. የቢሮ ኃላፊው ሥልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀፆች ከተገለፀው በተጨማሪ ቢሮ ኃላፊው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም አንቀጽ 43 (ሀ) ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ከተጣለው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል:: ሆኖም ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማኅበራዊ ወይም ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች ወይም በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 43(ሀ) ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከብር 50,000 (አምሳ ሺህ ብር) በላይ የሆነ የታክስ ክፍያ ነፃ ሊሆን የሚችለው በክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል::

c. The tax period or tax periods in which the offence occurred;

d. The amount or estimated amount of the tax evaded; and

e. The amount, if any, of the additional tax imposed.

PART SEVEN

Miscellaneous Provisions

33. Duty to Cooperate

1. All Federal and Regional Government Authorities and their Agencies, Bodies, Kebele Administrations and Associations shall have the duty to cooperate with the Tax Authority in the enforcement of this Proclamation.

2. a) No Ministry, Municipality, Department or office of Federal or Regional Government shall issue or renew any license to any taxpayer unless the applicant produces a certificate from the Tax Authority to the effect that tax due in respect of the preceding year or years, have been paid or where the taxpayer is seeking license for the first time taxpayer identification number (TIN) issued by the Tax Authority unless appeal is pending, or time for payments is extended by the Tax Authority.

b) If the Tax Authority refuses to issue a certificate it shall, on demand by the applicant for the license, provide him or it with a written statement of its reasons therefore.

C) Any applicant who is aggrieved by the reasons stated by the Tax Authority for refusing to issue a certificate or by the revocation of his or its license may appeal in writing to the Review Committee.

34. Powers of the Head of the Bureau

The Head of the Bureau may waive in whole or in part the tax levied under this Proclamation for reasons specified in under Article 43(a) of the Income Tax Proclamation No. 76/2002. However, for economic, social or administrative reasons or reasons specified in under Article 43 (a) of the Income Tax Proclamation, the amount of tax exceeding Birr 50,000 (fifity thousand Birr) shall be waived up on permission by the Council of the Regional Government.

35. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ሊያወጣ ይችላል።

36. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚወጡት ደንቦች ተፈፃሚነት የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

37. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ሳይከፈል የቀረ የኤክሳይዝ ታክስ በፌዴራሉ መንግስት የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 68/1985 ዓ.ም.በተደነገገው መሠረት የሚሰበሰብ ይሆናል።

38. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

35. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue regulations for the implementation of this Proclamation.

36. Power to Issue Directive

The Bureau may issue detailed directives help ful for the implmentation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamtion.

37. Transitory Provissions

All Excise Tax due prior to the coming into force of this Proclamation shall be paid in accordance with the Federal Government Sales and Excise Tax Proclamation No. 68/1993.

38. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 20th day of April, 2004

Yosef Retta
Presidant of the Amhara National Region

ሠንጠረዥ አገር ውስጥ በሚመረቱ የተወሰኑ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ ልክ	
የዕቃው ዓይነት	የኤክሳይዝ ታክስው በመቶኛ(%)
1. ማናቸውም ዓይነት ስኳር (በእንኳር መልክ) ሞላሰስን ሳይጨምር	33
2. መጠጦች	
2.1 ማናቸውም ለስላሳ መጠጦች (ከፍራ ጭማቂዎችና እነዚህንም ከመሰሰሉ በስተቀር)	40
2.2 በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ለስላሳ መጠጦች	40
2.3 በፋብሪካ የሚመረት የታሸገ ውሃ	30
2.4 ማናቸውም አልኮል ያለባቸው መጠጦች	
2.4.1 ማናቸውም ቢራና እስታውት	50
2.4.2 ማናቸውም የወይንጠጅ መጠጦች	50
2.4.3 ሌሎች አልኮል ያለባቸው መጠጦች	100
3. ማናቸውም ዓይነት ንፁሕ አልኮል	75
4. ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች	
4.1 የትምባሆ ቅጠል	20
4.2 ሲጋራት፣ ሲጋራ፣ ሲጋሪሎስ፣ የፒፖ ትምባሆ፣ ሱረትና ሌሎች የትምባሆ ውጤቶች	75
5. ጨው	30
6. ጨርቃ ጨርቅ እና ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ ዕቃዎች	
6.1 ከተፈጥሮ ሐር፣ ከራዩን፣ ከናይለን፣ ከሱፍ ወይም ከማናቸውም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች በሽራብ መልክ ቢሆን የተሠሩ ጨርቃ ጨርቆች፣	10
6.2 በሙሉ፣ ሆነ በከፊል የተሠራ አመድማ፣ ነጭ ቀለም የተነከረ ወይም የታተመ በማናቸውም ቁመት ወይም ወርድ የተሠራ ጨርቃ ጨርቅ (ከወባ መከላከያ አጎበር እና ከአቡጀዲ በስተቀር) እንዲሁም የብርድ ልብሶች አንሶላዎች፣ የአልጋ ሽፋኖች፣ ፎጣዎች የጠረጴዛ ልብሶች፣ እነዚህንም የመሰሰሉ ጨርቃ ጨርቆች፣	10
6.3 ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ ወይም የተዘጋጁ ልብሶች	10
7. ከወርቅ ከብርና ከለሌሎች ነገሮች የተሠሩ ጌጣጌጦች	20
8. የወለል ምንጣፎች	30
9. አስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውጤቶች	20
10. አሻንጉሊቶችና መጫወቻዎች	20

Type of Product	Excise Tax Rate (%)
1. Any type of sugar (in solid form) excluding molasses	33
2. Drinks	
2.1 All types of soft drinks (except furit juices)	40
2.2 Powder soft drinks	40
2.3 Water Bottled or canned in a factory	30
2.4 Alcoholic Drinks	
2.4.1 All types of beer &stout	50
2.4.2 All types of wine	50
2.4.3 Others alcoholic drinks	100
3. All types of pure Alcohol	75
4. Tobacco & Tobacco Products	
4.1 Tobacco Leaf	20
4.2 Cigarettes, cigar, cigarillos, pipe tobacco, snuff and other tobacco products	75
5. Salt	30
6. Textile and Textile products	
6.1 Textile fabrics, knitted or woven of natural silk, rayon, nylon, wool or other similar materials	10
6.2 Textile of any type partly or wholly made from cotton, which is grey, white, dyed or printed, in pieces of any length or width (except Mosquito net and "Abudgedid") and including blankets, bed sheets, counterpanes, towels, table clothes and similar articles	10
6.3 Garments	10
7. Personal adornment made of gold, silver or other materials	20
8. Carpets	30
9. Asbestos and Asbestos Products	20
10. Dolls and toy	20